

# 3-2

# ልዩ ልዩ የፈተና ደረጃ

ክርስቶስ አምላክ በመሆኑ ፈተና እንደ ሰው ይደርስበታል ብሎ መገመት በጣም አስቸጋሪ ነው። ሆኖም በሰው ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ፈተናዎች ሁሉ በክርስቶስ ላይ ደርሶበታል። በጣም የሚያስገርመው ነገር ክርስቶስ ፈተና ያጋጠመው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከተሞላና ከሰማይ “የምወደው ልጄ ይህ ነው” የሚለውን ደምጽ ከሰማ በኋላ ነው። ብዙ ጊዜ እኛም ከባድ የፈተና ግፊት ሊደርስብን የሚችለው አብዛኛውን ጊዜ በመንፈሳዊ ሕይወት አቋማችን በጥሩ ሁኔታ ላይ በመንገኝበት ጊዜ ነው። በመንፈሳዊ ሕይወታችን ባደግን ቁጥር የጠላትም ትግል በዚያው መጠን ጠንካራ እየሆነ ይሄዳል።

## 1. የሥጋ ፈተና

ክርስቶስ በሰይጣን መፈተን ሲጀምር የቀረበለት ፈተና የሥጋ ፈተና ነበር። በተራበና በተጠማ ጊዜ ስለ አገኘው *“…እነዚህ ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ በል አለው”* ማቴ. 4፥3። ምንጊዜም ቢሆን ሰይጣን ሰውን ለመጣል በሥጋዊ ፍላጎቱና ምኞቱ በኩል በቅድሚያ ይመጣበታል። በዚህኛው መስመር ጠልፎ መጣል ከቻለ ሌላ የፈተና ወጥመድ መዘርጋት አያስፈገውም። ይሄ የሰይጣን ዘዴ ዛሬ ብቻ የሚጠቀምበት አይደለም። ጥንትም በአዳምና በሄዋን ጊዜም ተጠቅሞበት ሲሠራ አይቶታል። አይሳካለት እንጂ በክርስ ቶስም ላይ ሞክሮታል። አልፎ አልፎ አማኞች በዚህ ፈተና ድል ስለሚመቱ፥ በውስጣቸው ልዩ ግጭትና ግፊት ይደርስባቸዋል። በዚያም ምክንያት አማኝ ሊኖረው የሚገባውን ደስታ፣ ሰላምና እርካት የጎደላቸው ይሆናሉ። ያንንም ደስታ ለማሟላት ከተገቢው በላይ በቆሳቁሳዊ ኃይል ብቻ ዝነኛ ሆነው ለመታየት ሲታገሉ ይታያሉ። ሰይጣን በዚህ ደረጃ ክርስቶስን መጣል ሲያቅተው በሌላ አቅጣጫ ሞከረ።

## 2. የነፍስ ፈተና

ሰይጣን ክርስቶስን በመቅደስ ጫፍ ላይ አውጥቶ *“…የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንህ ወደታች ራስህን ወርውር አለው”* ማቴ. 4፥6። በጥበብና በዘዴ የክርስቶስን አዕምሮ፣ ስሜትና ፈቃድ ለማሸነፍ ሞከረ። የመጽሐፍ ቃል በመጥቀስ ለአስተሳሰቡ የሚስማማ የሚመስል ሃሳብ በማቅረብ ሊያሸንፈው ሞከረ። አስደናቂና ትንግርት የሞላበት ድርጊት ቢፈጽም ተደናቂ እንደሚያደርገው ሃሳብ በማቅረብ ስሜቱን ለመቀስቀስ ሞክሮ ሳይሳካለት ቀረ። ይህንን ዘዴ ሰይጣን በዘመናችንም ባሉት አማኞች ላይ ይጠቀም በታል። በመጀመሪያ ለአእምሮአቸው የሚስማማ ሃሳብ ያቀርብላቸዋል። “ይህን የተማረና የተመራመረ ሰው ያደርገዋል” ይላቸዋል። አማኙም የሰይጣንን ዘዴና ጥበብ ካልተገነዘበ አዋቂነቱን ለማስመስከር ከክርስቶስ መንገድ የሚያስወጣውን ሥራ ያደርግ ይሆናል። ሰይጣን ለአእምሮአችን የሚመስለውን ሃሳብ ማቅረብ ብቻ ሳይሆን ስሜታችንንም መቀስቀስ ይችላል። እንግዲህ ሰው የሚፈተነው በሥጋው ብቻ ሳይ ሆን በነፍሱም ጭምር ነው። ነፍስም የሚያጠቃልለው አእምሮአችንን፣ ስሜታችንንና ፈቃዳችንን ነው። ስሜታችንንና አእምሮአችንን በማባበል ፈቃዳችንን ለመግዛት ይሞክራል።

## 3. የመንፈስ ፈተና

ሰይጣን ባለፉት ሁለት ዓይነት ዘዴዎች ክርስቶስን መጣል ሲያቅተው በሌላ አቅጣጫ ሊሞክረው ተነሳ። *“ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ”* አለው ማቴ. 4፥9። በዚህኛው ፈተና ክርስቶስ ወድቆ እንዲ ሰግድለት ሙከራ አደረገ። አምልኮት በመንፈስ በመሆኑ ሰይጣን ቀስ በቀስ መንፈሱን ለመያዝ ቢሞክርም ሳይሳካለት ቀረ። ይሄኛው ፈተና ካለፉት ሁለት ዓይነት ፈተናዎች የከፋ በመሆኑ፥ ማንኛውም ቅዱስ የሆነ ሰው እንኳን ሊወድቅበት ይችላል። ይሄ ፈተና አማኝን ወደ ተሳሳተ አምልኮት የሚከቱ ናቸው። አምልኮት ስንል በሃይማኖት ውስጥ ያለ አምልኮት ብቻ ሳይሆን ቁሳቁሳዊ አምልኮትንም ይጨምራል። ፈተናውም ወደ አማኝ የሚቀርበው የተለያየ መልክና አቋም ይዞ ነው። የእግዚአብሔርን ታላቅነት ረስቶ በራሱ እንዲታመን የሚገፋፋ ፈተና ነው። በራሱም ባይታመን ለጊዜያዊ ነገር ከእግዚአ ብሔር አስበልጦ ልቡን ሲሰጥ ሳይጣን በዚያ አማኝ ሕይወት ድልን ያገኛል። አማኝ ከክርስቶስ ይበልጥ የሚወደው ሌላ ነገር ካለ፥ ትክክል ባልሆነ አምልኮት ውስጥ የሚኖር መሆኑን መዘንጋት የለበትም። የሰይጣንም የመጨረሻው ከፍተኛው ተጋድሎ ሰው ወደ እግዚአብሔር እንዳይጠጋ ማድረግ ሲሆን፥ ሰው ዓይኑንና ልቡን የሚያሳርፍበትን ለጊዜው መልካም የሚመስሉትን ነገሮች ይደረድርለታል። ካለማወቅ የተነሳ ከእግዚአብሔር ይበልጥ ሌላ የምንወደውና የምናመልከው ነገር ይኖር ይሆን?

## በፈተናችን ለመጽናት …?

ፈተና ለመንፈሳዊ ሕይወት እድገት ጠቃሚ ቢሆንም ፈተና ውስጥ እየፈለግን እንገባለን ማለት አይደለም። እንዲያውም ክርስቶስ “ወደ ፈተና እንዳትገቡ ነቅታችሁ ጠብቁ” ሲል በጥብቅ ያስጠነቅ ቀናል። ፈተና በአማኝ ሕይወት ውስጥ መድረሱ የማይቀር ከሆነ፥ ታዲያ በምን ኃይል ማሸነፍ እንችላለን? ክርስቶስ “እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል” በማለት ሰይጣንን ለማባረር ከተጠቀመበት፥ እኛም አማኞች በፈተናችን ወቅት የእግዚአብሔርን ቃል በመጥቀስ ሰይጣንን ማሸነፍ እንችላለን። ቀጥሎም በፈተናችን አሸናፊ ሊያደርገን የሚችለውን ኃይል ወደሚለግሰው አምላክ መጠጋት ድል ከመመታት ያድነናል።

## 1. በቃሉ እንጠቀም

ክርስቶስ ተፈትኖአል፤ ሆኖም ኃጢአት አልሠራም።። እርሱ ከተፈተነ እኛም እንፈተናለን። ይበልጥ ችግር ያጋጥመናልና ፈተና ከማይደርስበት ስፍራ ለመሸሽግ ሙከራ አናድርግ። አመጣጡን አይተን መቋ ቋም እንድንችል፣ ፈተናችን ከየት፣ በምንና እንዴት እንዲሁም መቼ እንደሚመጣ በጥንቃቄ እንወቅ።

## 2. ለመደበቅ አንሞክር

ብዙ ጊዜ ፈተና ሲደርስብን እግዚአብሔርን ምክንያት እናደርጋለን። መጽሐፍ ቅዱስ ግን እግዚአብ ሔር ሰውን ለመጣል ወጥመድ እንደማይዘረጋ ይነግረናል (ያዕ. 1፥15)። አልፎ አልፎ ደግሞ “ሰይጣን አብዝቶ ስለፈተነኝ በኃጢአት ወደቅሁ” በማለት በሰይጣን ለማመካኘት እንሞክራለን።ያም ሆነ ይህ ግን የምንሰጣቸው ምክንያቶች ሁሉ በደለኞች እንዳንሆን ንጹህ አያደርጉንም።

## 3. በአምላክ እንታመን

በ1ኛ ቆሮንቶስ 10፥13 መሠረት ሶስት ዓይነት ተስፋዎች ተሰጥቶናል።

1. በሰው ያልደረሰ ዓይነት ከፉ ፈተና እንደማይደርስብን
2. ከምንችለው በላይ ፈተና እንደማይደርስብን
3. ለፈተናችን ሁሉ እግዚአብሔር መውጫውን እንደሚያዘጋጅልን የእግዚአብሔር ቃል ያረጋግጥ ልናል። እንግዲህ የእግዚአብሔር መንገድ በፈተናችን ወቅት መሸሽ ሳይሆን መታገስ ነው።

## በፈተናችን ብንወድቅስ?

እንደ እውነቱ ከሆነ በሚያጋጥመን ፈተና ሁሉ እናሸንፋለን ማለት አይደለም ታዲያ በፈተናችን ማሸነፍ አቅቶን ኃጢአት ትንሠራ ምን ማድረግ አለብን? ቀደም ሲል ወደ ክርስቶስ ስንመጣ እንዳደረግነው በእግዚአብሔር ጸጋ በመታመንና በመደገፍ ኃጢአታችንን መናዘዝና ይቅርታ መጠየቅ አለብን። *"ምሥራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ፥ እንዲሁም ኃጢአታችንን ከእኛ አራቀ"* (መዝሙር 103፥12)።

**የጌታ ጸጋና ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን። አሜን!**